በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ አሜን!

# ምሥጢራተ

# ቤተክርስቲያን

# 2. ምሥጢረ ሜሮን

ምሥጢረ ቅብዓ-ሜሮን አንድ ምእመን/አማኝ/ሕፃን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ እንዳበቃ በጥምቀት ያገኘው ዳግም ልደት (አዲስ ሕይወት) ቅዱስ ዘይት በመቀባት የሚታተምበት (የሚረጋገጥበት) እና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የሚቀበልበት ሥርዓት ነው።

- ‹‹… በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ - በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው›› ኤፌሶን 1፥13-14

- ‹‹ ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ›› ኤፌሶን 4፥30

# አንብሮተ ዕድ እና ቅብዓ-ሜሮን

በሐዋርያት ዘመን ተጠማቂዎች ከተጠመቁ በኋላ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉት ሐዋርያት እጃቸውን እየጫኑባቸው (በአንብሮተ እድ) ነበር (ሐዋ 8፥17፤ 19፥5-6፣)።

- ‹‹… ተጠምቀው ነበር እንጂ (መንፈስ ቅዱስ) ከእነርሱ በአንዱ ላይ ገና አልወረደም ነበርና። በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ›› ሐዋ 8፥17
- ‹‹ይህንንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ። ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው…›› ሐዋ 19፥5-6

# አንብሮተ ዕድ እና ቅብዓ-ሜሮን…

- ቤ/ክ እየተስፋፋች እና ምእመናን እየበዙ ሲሄዱ ሐዋርያት በሁሉም ቦታ በአካል ተገኝተው እጅ መጫን ስላልቻሉ በአንብሮተ እድ ፈንታ ቅብዓ-ሜሮንን ተክተዋል፡፡
- ‹‹እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡ … እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፡፡ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፣ እውነተኛም እንደሆነ፣ ውሸትም እንዳልሆነ፣ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ›› 1ዮሐ 2፥20፥ 27
- ‹‹በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናን እና የቀባን እግዚአብሔር ነው፡፡ ደግሞም ያተመን፣ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው›› 2ቆሮ 1፥ 21-22

# የቅብዓ-ሜሮን አዘገጃጀት እና አፈጻጸም

- ሜሮን በሊቃነ-ጳጳሳት እና በጳጳሳት በሚመራ ልዩ የጸሎት ሥነስርዓት (በቅዱስ ሲኖዶስ) ከእጽዋት (በተለይም ከወይራ ዘይት) ተቀምሞ የሚዘጋጅ ሲሆን ለአብያተ ክርስቲያን እየታደለ ተጠማቂዎች ወዲያው ተጠምቀው እንደወጡ በካህኑ የሚቀቡት ቅዱስ ዘይት ነው። በመሆኑም እንደጥምቀት ሁሉ ሜሮን አይደገምም።

- ሥርዓቱንም የመፈጸም (የመቀባት) ሥልጣን ያላቸው ጳጳሳት እና ቀሳውስት ብቻ ናቸው።

- ከዚህም ሌላ በቤ/ክ ሥርዓት ጳጳሳት እና ነገሥታት ሲሾሙ፣ እንዲሁም ደግሞ አዲስ ሕንጻ ቤ/ክ እና አዳዲስ ንዋያተ ቅድሳት ሲባረኩ ቅብዐ-ሜሮን ይቀባሉ።

# ቅብዐ-ሜሮን በብሉይ ኪዳን

- ይህ ቅብዐ-ሜሮን በብሉይ ኪዳን ስም ባይሰጠውም ቅሉ ሌዋውያን ካህናት ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ይገለገሉበት ነበር፡፡ ለምሳሌ፡-

- ንዋየ ቅድሳትን ለማክበር (ለመባረክ)፡-

  ‹‹… የተቀደሰም የቅባት ዘይት ይሆናል፡፡ የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት… ዕቃውንም ሁሉ… ትቀባበታለህ፡፡ ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ›› ዘጸአት 30፣ 25-29

- ካህናትን ለመሾም (ለመባረክ)፡-

  ‹‹… በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮን እና ልጆቹን ቅባቸው፤ ቀድሳቸውም፡፡ እንዲህ ብለህም ተናገር ይህ- ‹ለልጅ ልጃችሁ የተቀደሰ የቅባት ዘይት ይሁንልኝ›…›› ዘጸአት 30፣ 30-32

# ቅብዐ-ሜሮን በብሉይ ኪዳን...

- ‹‹ሙሴም ከቅባቱ ዘይት … ወስዶ በአሮንና በልብሱ ላይ፣ በልጆቹና በልጆቹ ልብስ ላይ ረጨው፤ አሮን እና ልብሱንም፣ ልጆቹንና የልጆቹን ልብስንም ቀደሰ›› ዘሌ 8፣30

- ነገሥታትን ለመሾም:-

  ‹‹… እግዚአብሔርም ይህ ነውና ተነስተህ ቅባው አለው:: ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው:: የእግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ›› 1ሳሙኤል 16፣13 (የሳኦልን መቀባት:- በ1ሳሙኤል 10፣1 ይመልከቱ)

- ‹‹ካህኑም ሳዶቅ ከድንኳኑ የቅብዓቱን ቀንድ ወስዶ ሰሎሞንን ቀባ፤ ቀንደመለከትም ነፉ፤ ሕዝቡም ሁሉ- ‹ሰሎሞን ሺህ ዓመት ይንገሥ› አሉ›› 1ነገሥት 1፣39

ወለእግዚአብሔር ስብሓት!